# የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ

# (ት.ዴ.ፓ)

ፕሮግራም
(በመስራች ጉባኤ የፀደቀ)

ኅዳር 27, 2012 ዓም

# የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ
## ፕሮግራም

### *መግቢያ*

ጥንታዊትዋ ኢትዮጵያ የየራሳቸው ስልጣኔና ስርአተ መንግስት መስርተው ይተዳደሩ ከነበሩት ጥቂት ቀደምት ሃገሮች አንድዋ ለመሆንዋ ሃውልቶችዋ፥ ፊደሎችዋ፥ ቀን መቁጠርያውና መዛግብቶቹ ሊያስረዱ ቢችሉም አሁን ያለችው ኢትዮጵያ ግን እጅግ ወደ ኃላ የቀረች አገር ሆና ትገኛለች። የተፈጥሮ ሃብትዋና ብቃት ያለው የሰው ሃይልዋ ኣጥጋቢ እድገት ሊፈጥር የሚችል ሆኖ እያለ፣ የኣስተዳደር እጦት ባስከተለው መዘዝ ህዝብዋ በድህነትና ስቃይ የሚኖርባት፥ ገዢዎችዋ ግን ተዝናንተው የሚፈነጩባት ሃገር ሆና ትገኛለች።

ኢትዮጵያ አገራችን በዓለም ላይ በጣም ኃላ ቀር ተብለው ከሚታወቁት ጥቂት አገሮች አንዷ ናት ። ከዚህ በፊት ህዝቡን ሲያሰቃዩት የቆዩ በሽታ፣ ድርቅ፣ ወረርሽኝ፣ ረሀብ፣ መሃይምነትና ጦርነት አሁንም እንዳሉ ናቸው ። ኣንዳንዶቹ ችግሮችም ብሶባቸዋል። የአገሪቱን ህልውና እስከማናጋት የደረሰውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና፣ ፖለቲካዊ ከባድ ቀውስ ከተከሰተ ኣመታት ያስቆጠረ ቢሆንም በኢትዮጵያ እየመጡ ያለፉት መንግሥታት ይህን ኣስከፊ ተርእዮ ለመለወጥ ያደረጉት ሙከራ በጣም ዝቅተኛ ወይም ኣቅጣጫውን የሳተ ነበር ማለት ይቻላል ።

ባለፉት ሃምሳ ኣመታት እንደተገነዘብነው የኢትዮጵያ መንግሥታት ያደረጉት አስተዋጽኦ ቢኖር አሉታዊ ክስተቶችን መጋበዝና የራሳቸውን ዘላቂ የምቾት ኑሮ ማስተካከል ብቻ ነው ። ዛሬም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ተጽዕኖዎችን ለማስወገድ ቃል ገብቶ ለሃያ ዓመታት ያህል ከፍተኛ መሰዋዕትነትን የጠየቀ ጦርነት በማካሄድ ሥልጣን የተረከበው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) መንግሥትም ቢሆን ካለፉት መንግስታት የተሻለ ለመሆን ያደረገው ሙከራ የለም ። እንዲያውም እስካሁን የተከተለው ኣምባገነናዊ ኣመራር አገሪቱን ወደ ባሰ ኣዘቅት ከትዋት ይገኛል።

የኢትዮጵያ ህዝብ አገሩን ለማበልጸግ፣ ራሱንም ለመመገብና መሠረታዊ የሆኑ የጤና፣ የትምህርት፣ የሰላምና ልማት የመሳሰሉትን ችግሮች ለማሸነፍ በህዝባዊ ውክልና በጸደቀ ህግ መሠረት የሚያስተዳድረውን ፓርቲ ለመምረጥ የሚያስችል ሁሉን ኣቀፍ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መዋቅሩን መመሥረት ተቀዳሚ ፍላጎቱ ነው ። በዚህም መልክ የተመረጠውን ፓርቲም ይሁን መንግሥት በሠራው ሥራ ለማመስገንም ሆነ ለማስተካከል ኣልያም ለማስወገድ እንዲቻል ማድረግ ምንጊዜም የህዝቡ መሰረታዊ ፍላጎት ነው። ባለፉት 27 ዓመታት የህዝቡን ፍላጎት በመጻረር ኢህኣዴግ ኣምባገነናዊ ማነቆ በማበጀት ራሱ በስልጣን ላይ ለማቆየት ብቻ የሚጠቀምበት ስርኣት ዘርግቶ ይገኛል። ህዝቡም ነጻ ሆኖ፥ ተንቀሳቅሶ፥ ጥሮ ግሮ ችግሮቹን እንዳይፈታና ሃገሩን እንዳያበለጽግ ታፍኖ ቆይቷል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ያለፈውን የወታደር መንግሥት በማስወገድና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት ባደረገው ትግል ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለዋል። ይሁን እንጂ በህዝብ ለተነሱት ጥያቄዎች በማፈን ካለፉት ዘመናት ጥፋቶች መማር ያልቻለው ኢህአዴግ አገሪቱን ወደ ባሰ ችግርና ወደ ሌላ ብጥብጥና አለመረጋጋት ከቶታል። ምንም እንኳ የደርግን ስርአት አስወግዶ ለውጥ ለማምጣት ከባድ መስዋእትነት ቢከፈልም፣ ይህ መንግሥት ታገልኩልህ ለሚለው የትግራይን ህዝብ ይሁን ባጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማፈን ከፍተኛ ችግሮችን ፈጥሯል። ከመቸውም ጊዜ በባሰ መልኩ በህዝቦች መካከል ልዩነቶችን በማጉላት መቃቃርና ግጭት እንዲስፋፉ

በማድረግ ለብዙ ህዝብ ሕይወት መቅዘፍት ምክንያት ሆኖዋል። አንዳዶች የዚህ ችግር ምንጭ ኢህአዴግ የፌደራል ስርዓቱን በብሄሮች(በዘር) ማዋቀሩ ነው የሚሉ አሉ። ትዴት ይህንን አመለካከት አይጋራም። በወቅቱ ኢትዮጵያን በጋራ ለማቆየት የነበረው ተጨባጭ አማራጭ ለብሄሮች መብት መስጠትና ተስማምተው በጋራ ፌደራል ስርዓቱን መገንባት ብቻ ነበር። ችግሩ በፌደራል መዋቅሩ ሳይሆን መዋቅሩን ለመጠበቅና ለማስቀጠል የሚያስችል ዲሞክራሲያዊ ስርዓት አለመኖሩ ነው። አሁንም ትዴት ያለውን መዋቅር ተቀብሎ ሁሉም ብሄሮች ተማምነውና ተከባብረው ሊሄዱበት የሚችሉበትን ዲሞክራሲያዊ ስርአት እንዲፈጠር እና የሚያስተሳስራቸው የጋር ታሪክና ለወደፊትም የጋራ ጥቅም እንዳላቸው በማመን ይታገላል።

በህዝቦች መካከል መቃቃርና ግጭት ካለ እድገትና በሰላም ኣብሮ መኖርም ስለማይታሰብ፥ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር ይህን ኣደገኛ ኣዝማምያ ለመቀልበስና በህዝቦቹ መካከል የነበረውን ሰላማዊው ዝምድና ለማስፈን እንደ ድልድይ ሆኖ ለማገዝና፥ እንዲሁም ፍትሕና ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በኢትዮጵያችን ለመገንባት የተደራጀ ሃይል ነው ። ስለሆነም ኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖር የሚገባው መንግሥት የሁሉንም የፖለቲካ ፓረቲዎች ኣመኔታ ባገኘና ህዝቡ ባጸደቀው ሕገህዝብ (ሕገመንግስት) ስልጣን ላይ የሚወጣና የሚወርድ እንደዚሁም የሚመራ መሆን ኣለበት ይላል። ሁሉንም በሰላማዊ መንገድ ለማሳተፍ የሚያስችል ፖለቲካዊ መድረክ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀርበው የህዝብ ድምጽ ለማግኘት የሚወዳደሩበት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር በጽኑ ይታገላል ። የብዙኃን ፓርቲ ዴሞክራሲ፣ በህዝባዊ ምርጫ የድምጽ ብዛት ያገኘው የአንድ ወይም የጥምር ፓርቲዎች ሥልጣን አስተዳደርን የመመሥረት አቋም የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር ዋነኛ ከሆኑት የትግል መርሆ ኣንዱ ነው። ልዩነቶች በፖለቲካ መስመሮች ብቻ ሳይወሰኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበረሰባዊና ሥነ ህሊናዊ ዝንባሌዎችም ጭምር ያካተቱ በመሆናቸው ስልጣን የሚረከበው ወገን የህዝብን ኣደራ ለመወጣት እንጂ ተቀናቃኙን በማንኛውም መንገድ ለማጥቃት መልካም አጋጣሚ እንደተገኘ የሚቆጠርበት አመለካከት እንዳይኖር ምንጊዜም ይታገላል። ጸረ እድገትና ሰላም ኣመለካከቶች ለኣምባገነኖች መረማመጃ መሳልል እንዳይሆኑ የጋራ ዲሞክራሲያዊ ስርኣት፥ ህግጋቱና ደንቡ ጭምር በህብረት በቅድሚያ እንዲመሰረቱ ማድረግ የግድ ይላል ።

ሌላው የሚታየው የፖለቲካ ችግር የብሔር/ብሔረሰቦች ጥያቄን በተመለከተ ነው ። ባለፉት የኢትዮጵያ መንግሥታት እየተካረረ የመጣው የብሔሮች ቅራኔ አሁንም ዘላቂ መፍትሔ አላገኘም። ቅራኔው ገዢዎች የፈጠሩትና ለከፋፍለህ ግዛ የሚገለገሉበት ቢሆንም የተፈጠረው ልዩነት በተለያዩ የአገሪቱ ህዝቦች መካከል ቢያንስ እርስበርስ መጠራጠርን ፈጥሯል ። ሰዎች የነበረውን ታሪካዊ ዝምድና እንዳልነበረ፥ ያልነበረው ደግሞ እንደነበረ ኣድርገው የማቅረብ ኣዝማምያዎች ታይቶባቸዋል። የኢህአዴግ መንግሥት ችግሩን በመረዳት የተፈጠሩትን ልዩነቶች በማርገብና በመፍታት ፈንታ ሲያባባሳቸው ቆይቷል ። በተለይም የሚያሳስበው በህዝቦች መካከል የታዩትን ቅራኔዎች ኣንዱን በመደገፍና ሌላውን በማጥላላት ወደ ባሰ ግጭት እንዲያመሩ በህወሓት የሚመራው መንግሥት መሳርያ ኣድርጎ ሲጠቀምበት መቆየቱ ነበር። በተከታታይ የነበሩት ገዢዎች የብሄሮችን ቅራኔ በማባባስና ህዝቡን እርስበርስ በማጋጨት የግዛት እድሚያቸውን ለማራዘም የተጠቀሙበት ስለሆነ ብሄራዊ ቅራኔው መፍትሄ የሚፈልግ ኣንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑን የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር ኣበክሮ ያምንበታል። ለብሄራዊ ጭቁና መፍትሄው ታግሎ ጭቆናን ማስወገድ እንጂ መገንጠል መፍትሄ ኣለመሆኑንም ያምናል። የኢትዮጵያ ህዝቦች በ89ኙ ብሔረሰቦች ቢገነጣጠሉ ለችግሮቻቸው መፍትሄ ተገኘ ማለት ኣይደለም። ጥያቄው የእኩልነት፥ የመከባበር፥ ባጠቃላይ የሰብኣዊና ዴሞክራስያዊ መብቶች መከበር ሆኖ መፍትሄውም ለነዚሁ መብቶች መከበር ታግሎ ፍጻሜ ላይ ማድረስ ነው። እንደነዚህ ጥልቀት ያላቸው የፖለቲካ ችግሮችንም በመገንዘብና በብሔሮች መካከል መሰረታዊ ቅራኔ እንደሌለ በመረዳት የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት) በብሔሮች እኩልነትና መከባበር እና በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተመሰረተ ፌደራል መንግስት የጸና አቋም ይዞ እውን እንዲሆን በተግባር ይታገላል ።

ኢኮኖሚያዊ ኃላ ቀርነት ከሰው ልጅ የተዛባ አስተዳደር ተዛምዶ የሚፈጠር ተርእዮ ነው። ኣልፎኣልፎ የሚከሰት የተፈጥሮ ኣደጋ ኣሉታዊ ሚና መጫወቱ የታወቀ ቢሆንም መልካም ኣስተዳደር እስካለ ድረስ ችግሩን በቀላሉ ሽሮ ቀጣይነት እድገት እንዲኖር ለማድረግ ይቻላል ።

በርግጥ ለዘመናት በሽታና ረሀብ የኣብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የዕለት ኑሮ ሆኖ ቆይተዋል። በኣሁኑ ወቅት ደግሞ ሥራ አጥነቱና የኑሮ ውድነቱ በጣም ከፍ ብሎ የሚታይበት ሁኔታ ነው። የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ከነዚህና ተያይዘው ከተከሰቱት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመላቀቅ አጣዳፊ መፍትሔ ያስፈልገዋል። መፍትሔዎቹም በህዝብ ልበ ሙሉ ተሳትፎና ፥ ይህንን ፈታኝ ችግር ለማስውገድ የህዝቡ ኣለኝታ ያገኘ ቆርጦ የተነሳ መንግሥት በሚያሳየው ፍትሃዊ ፖሊሲና ቅን ፍላጎት የሚመንጩ ይሆናሉ። በሥልጣን ላይ ያለው የኢህኣደግ መንግሥት በየአመቱ በ11% እድገት አመጣሁ እያለ የውሸት ፕሮፖጋንዳውን ቢነዛም ከላይ የተጥቀሱትን የአገሪቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መሠረታዊ ለውጥ ማምጣቱ ወይም መቅረፉ ቀርቶ እያባባሰው ለመሆኑ በመሬት ላይ ያለው ተጨባጭ ሓቅ ያረጋግጣል።

ይህ ለዘመናት መሻሻልን ያላሳየ ኢኮኖሚ ላይ ፈጣን ለውጥ ለማምጣትና ተያይዘው ያንሰራሩት ኣያሌ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ለመፍታት ትክክለኛው ኣቅጣጫ ማወቁና መያዝ እንዲሁም ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ጋር በህብረት ካልሆነ በስተቀር በተናጠል የማይቻል እጅግ ከባድና ውስብስብ ስራ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ከጅምሩ ትክክለኛ ኣቅጣጫ ካልተያዘ መድረሻው ኣይታወቅም። ይህን ኣገር ኣድን መፍትሄ መሰረት ለማስያዝና የሰው ልጆችን ችግር ለማቃለል የሚረዱትን ፖሊሲዎች ያለምንም ቀኖናዊነት በተግባር ለመተርጎም ት.ዴ.ት. ቆርጦ ተነስተዋል። የኣፈጻጸሙ መመርያም ቀጥሎ በሚቀርበው ዝርዝር የፕሮግራም ይዘት ተገልጸዋል።

በአይዲዮሎጂ በኩል በዚህ ሚእተ አመት በዋነኛነት ተፎካካሪ ሆነው የቆዩት ሊበራል ካፒታሊዝም፣ ኮሙኒዝም/ሶሺያሊዝም እና ሶሺያል ዲሞክራሲ ናቸው። ኮሙኒዝም በሁሉም የተሞከረባቸው አገሮች፣ በአገራችንም ጭምር ጭርሽ ዲክታተሪያዊ ስርዓት በመፍጠር ውድቀትን ያስከተለ መሆኑ ነው የታየው። ሊበራል ካፒታሊዝም አሜሪካን የመሰለ በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ያደጉ አገሮች የፈጠረ ቢሆንም ፍትሃዊ የሆነ የሃገር ሃፍት ክፍፍል ባለመኖሩ ጥቂት ሃብታሞች የአገሪቱን ሃፍት ሲቆጣጠሩ አብዛኛው ህዝብ ደግሞ ኑሮ መግፋት አቅቶት ሲታገል የሚኖርባት፣ ፍትህ ለባለሃፍት ያደላበት አገር ሆናለች። ፎርብስ (Forbes)በኅዳር 2010ዓም(Nov.17,1917ዓምፈ) the Institute for Policy Studies የተባለው የጥናት ኢንስቲትዩት ያወጣውን መረጃ በመጥቀስ 3 የአሜሪካ ሃፍታሞች ብቻ የግማሹን የዝቅተኛው ክፍል አሜሪካዊ( 160 ሚሊዮን ህዝብ) ያህል ሃፍት አላቸው። የአሜሪካው ሊበራል ካፒታሊዝም በሃፍታምና በድሃው/በመሃከለኛው ሰው ያለውን ልዩነት እያሰፋ የሚሄድ፣ ሃፍት ወደ ጥቂት ግለሰቦች እይተጠቀለለ አባዛኛው ህዝብ የሚደህይበትና የሚሰቃይበት ሆኗል። ከነዚህ ከተጠቀሱት ሁለቱ ስርዓቶች የተሻለ ፍትሃዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ያሳየው በአውሮጳ በተለይ በስካንዲናቪያን አገሮች የታየው ሶሺያል ዲሞክራሲ ነው። በሶሺያል ዲሞክራሲ የግል እና የመንግስት ሃብት የሚመራ ኢኮኖሚ ሆኖ በተለይ መንግስት መሰረታዊ የሆኑትን የሕብረተሰቡን ፍላጎትና ግልጋሎት(እንደ ትምህርት ቤት፣ ህክምና፣ ትራንስፖርት፣ ቤት፣ የስራ እድል መፍጠር፣ ወዘተ.) በሚሟላት ላይ ሃላፊነት ይወስዳል። መንግስት ሃፍታሞች/ካፒታሊስቶች እንዲሰሩ ቢፈቅድም የአገሪቱ ሃፍት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በግብር እንዲሁም የስራተኛውን ደሞዝ ከፍ እንዲል በማድረግ ለህዝቡ እንዲዳረስ ያደርጋል። የአገሪቱ ኢኮኖሚም ገበያ እንደፈለገው የሚዘውረው ሳይሆን በፕላንና እቅድ እንዲመራ ያደርጋል። በፖለትካ አመራሩም ሊበራል ዲሞክራቲክ ነው። ትዴትም ይህንን የሶሽያል ዲሞክራሲ አይዲዮሎጂ ይከተላል። ዝርዝሩ በፕሮጋርሙ ላይ ሰፍሯል።

በትግራይም ሆነ በመላው የኢትዮጵያ ግዛት አስቸኳይና ጊዜ የማይሰጡ ችግሮች ስራአጥነትና ሙስነት ናቸው። ከህዝቡና ከኢኮኖሚው እድገት አኳያ ሲነጻጸር በየዓመቱ የሚጨምረው የስራአጡ ብዛት በጣም ከፍተኛ ነው። በትክክል ቁጥሩ ይታወቅል ባይባልም የስራአጡ ብዛት እስከ 50% መሆኑና በገጠርም በከፊል ስራአጥ ወይም ሙሉ በሙሉ በስራ ላይ ያልሆነ ሃይል እስከ 85% መሆኑ አንዳንድ

ዘገባዎች ያመላክታሉ። ይህ ችግር በአጭር ጊዜ የሚፈታ ባይሆኑም ችግሩን ለዘብ ለማድረግ አፋጣኝ መፍትሔዎች ያስፈልጋሉ። እርሻ ከ80% የሚሆነውን ህዝብ የያዘ በመሆኑ የአርሶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻል ቅድሚያ መሰጠት አለበት። የውሃ ቁጠባና የመስኖ ስራ ቀዳሚነት ተሰጥቶት ጥናትና እቅድ ማውጣትና በተግበር ማዋል ያስፈልጋል። ከእርሻውም ጋር ተያይዞ ሊስፋፉ የሚችሉ ፋብሪካዎች ይኖራሉ። ይህ የህዝቡን ኑሮ ካማሻሻል ባሻገር ከገጠር ወደ ከተማ የሚመጣውን የስራ ፈላጊ ሰውንም ይቀንሳል። በተጨማሪም የቤተሰብ ፕላኒንግ(family planing) ትምህርት መስጠትም የህዝቡ እድገት ከኢኮኖሚያዊ እደገቱ ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን በማድረግ ደጋፊ ውጤት ሊሰጥ ይችላል።

ሌላው ገንዘብ የማናወጣበትና የህዝባችን ቁርጠኝነት የሚጠይቀውን ሙስናን መቆጣጠር ነው። ባለፉት 27 ዓመታት ከኢትዮጵያ ያለአግባብ ወደ ውጭ የወጣው/የተሰረቀው ገንዘብ $36 ቢልዮን (የአሜሪካ ዶላር) መሆኑ ይገለጻል። ግሎባል ፋይናንሺያል ኢንተግሪቲ(Global Financial Integrity) የሚባለው ድርጅት በፈረንጅ አቆጣጠር በዲሰምበር 05, 2011ዓም ባወጣው ሪፖርት በፈረንጅ ከ2000 እስከ 2009 ዓም ማለትም በ10 ዓመት ወስጥ ከኢትዮጵያ ያለአግባብ የወጣው ገንዘብ 11.7 ቢልዮን የአሜሪካ ብር መሆኑን ይገልጻል። ከዚሁ ሌላ በአገር ውስጥ በጉቦ የሚመዘበረው ገንዘብ መመዘኛ የለውም። ይህን በሙስና የሚጠፋው የገንዘብ መጠን ስንመለከት ለአገሪቱ እድገት ምን ያህል ትልቅ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንድሚችል መገመት አያዳግትም። ይህ ሁኔታ በአጭር ጊዜ ማቆም አለብን። መንግስት በህግ መቆጣጠር እንዳለበት የማያከራክር ቢሆንም በቁጥጥር ላይ ህዝቡ ወሳኝ ሚና እንዳለው በመገንዘብና ህዝቡን ማስተማርና መቀስቀስ ያስፈልጋል። ህዝቡ፣ጋዜጠኛው፣ ሲቪክ ማህበሮች፣ ባለሙያዎች፣ ወዘተ. ሙስናን ለማጋለጥና ለማጥፋት ሚናቸውን እንዲጫወቱ መጀመሪያ ዲሞክራቲክ ስርዓት መፍጠር ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ አለብን። ህዝቡ ያለፍራቻ ማጋለጥ ሲችልና ፍርድ ቤቶችም ያልምንም ጫና ህግ ለማስፈጸም ሲችሉ ብቻ ግባችንን ልንምታ እንችላለን። ትዴት ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በሙሉ ቁርጠኝነት ይነሳል አስፈላጊው መዋቅር፣ ህጎችና ደንቦች አንዲዘጋጁም ያደርጋል።

የአገር ደህንነትን በተመለከተ የውጭ ወረራን ሊመክት የሚችል አስተማማኝ የአገር መከላከያ ኃይል በአንድ በኩል፥ በሌላው በኩል ደግሞ የህዝቡን ሰላምና ሕገ መንግስታዊ መብቶችን የሚያስከብር የፖሊስ ኃይል ሕብረ ብሔራዊ ተዋጽኦ ባለው ይዘት ማቋቋም የግድ ይላል። የመከላከያ አባልና ፖሊስ የማንኛውም ፓርቲ አባል አይሆንም። ዜጋዊ መብትና ግዴታ ሆኖ በዚህ መስክ አገሪቱ ሰላም፥ መረጋጋትና ዕድገት በዘላቂነት እንድትጎናጸፍ ሁሉም ዜጋ መተባበር ይኖርበታል ብሎ ትዴት ያምናል ።

ይህ ፕሮግራም በይዘቱ በመጀመርያ በየካቲት 1987(February 1995) ከወጣው የተለየ አይደለም። መግቢያው ላይ ካለው ሁኔታ ጋር ለማዛመድ አንዳንድ ማስተካከያዎች ተደርጓል። እንዲሁም በኢኮኖሚ ፕሮግራሙ ላይ ቁ. 2 እና ቁ. 3 ጨምሯል።

ሕዳር 2012 (December 2018)

**ክፍል 1**

**የፖለቲካ ፕሮግራም**

1. ዓላማው የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑ የሚረጋገጥበት፥ የሕግ የበላይነት የነገሰበት፥ የዜጎች ግላዊም ይሁን ስብስባዊ መብቶች የሚከበርበት ዘለቄነት ያለው ዴሞክራሲያዊ ስርኣት መመስረት ነው።

2. በሁሉም ፖለቲካ ሃይሎች፥ ሙያና ሲቪክ ማህበራት እንደዚሁም ሕገ መንግስታዊ ጠበብት ተረቆ በሞላው ህዝብ ተሳትፎ የጸደቀ ሕገመንግስት የሃገሪቱ የበላይ መመርያ ይሆናል።
3. ሶስቱ መሰረታዊ መንግስታዊ ኣካላት፣ ሕግ ኣውጪ፥ ተርጉዋሚና ኣስፈጻሚ ሕገ ደንቡ ለያይቶ በሚሰጣቸው የስራ ድርሻ ተገድበው ይሰራሉ። ሕግ ተርጓሚው ፍርድ ቤት ከማንኛውም ኣካል ተጽእኖ ፍጹም ነጻ ሆኖ ፍትህ እንዲነግስ ያደርጋል።

4. የብዙኃን ፓርቲ ፓርላሜንታዊ ሥርዓት ሆኖ፥ ሁለት ዘርፍ ያለው ምክር ቤት/ፓርላማ ይቋቋማል። ኣንዱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህዝብ ብዛትን መሰረት ያደረገ ውክልና ይኖረዋል። ሁለተኛው የፌደራል ምክር ቤት ከየራስ ገዝ ክልሎች ትንሽም ትልቅም ብሄር ይሁን ሁሉም በእኩል ቁጥር የሚወከሉ ይሆናሉ። እነዚህን ወኪሎች ህዝብ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫን በመጠቀም በቀጥታ ይመርጣቸዋል። የሁለቱም ዘርፎች ስልጣንና መብት እንዲሁም ያላቸው ግኑኝነት በህግ ይወሰናል። ትዴት አሁን ያለው ህገ መንግስት በዚሁ መንገድ እንዲስተካከል ይሰራል።

5. መሠረታዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ መርሆዎችን ማለትም የመናገር፥ የመሰብሰብ፥ ሀሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ነጻነቶችን፥ ገለልተኛና ሁሉን ያለ አድልዎ ሊያሳትፍ የሚችል የመገናኛ ብዙኃን መኖር፥ ሰላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም፣ አድማ የማድረግና በነጻ የመደራጀት መብትንም ጭምር በተግባር ያውላል ።

6. ሰዎች በሙያም ሆኑ በሲቪክ ማህበራት ከፓርቲና ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ ሆነው የመደራጀት መብቶቻቸውን ያከብራል ።

7. የብሔሮችና ብሔረሰቦች የራሰን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ያከብራል፥ ይጠብቃል ።

8. የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ከሚለያዩዋቸው ይልቅ የሚያስተሳስርዋቸው የጋራ ታሪካዊ፥ ባህላዊ፥ ማህበረ ኢኮኖምያዊ ሃረጎች ስለሚያይሉና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ህዝቦች ተለያይተው ሳይሆን በአንድነታቸው የሚያገኙት ጥቅም ስለሚበልጥ፥ በነዚህና በመሳሰሉ ምክንያቶች በመፈቃቀድ ላይ ለተመሠረተ አንድነትን ይቆማል ይታገላል።

9. በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን የማንኛውም ብሔር ብሔረሰብ ባህልና ታሪክ ማስፋፋትና ማቀብ በሕግ ይደግፋል ።

10. ት.ዴ.ት አሁን ባለው ሁኔታ በብሄር የተዋቀረውን ክልሎች ይቀበላል። ለወደፊት ግን የብሔር ክልል ሳይሆን የክልሎችን ኢኮኖሚያዊ እድገትና የህዝቦችን አንድነት በሚያጠናክር መንገድ በቂ ጥናት ተደርጎ፣ ህዝብንም በዲሞክራሲያዊ መንገድ ያሳተፈ ሆኖ እንዲቀናጅ ይደግፋል።

11. ሃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ ሆነው ኣንዱ በሌላው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት በሕግ የተከለከለ ይሆናል። የእምነት ነፃነት ይከበራል ።

## ክፍል II

### የኢኮኖሚ ፕሮግራም

1. እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ህዋላ ቀር አገሮች ውስጥ መንግሥት ከማንም ግለሰብ የበለጠ በብሔራዊ ሃብት ላይ የማዘዝ ችሎታና የማስተባበር ኣቅም ስላለው ሃገሪቷ ውስጥ ሊኖር ለሚገባው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና መጫወት አለበት ። የግል ሃፍታሞች በኢኮኖሚው ነጻ ሆነው እንዲሳተፉ ይፈቅዳል። ለህዝብ ግልጋሎት የሚሰጡና ለእድገትም አስፈላጊ በሆኑ ኢንፍራስትራክቸሮች ላይ መንግስት ኢንቨስት ያደርጋል። ስለዚህ የመንግሥትና የግል ካፒታል በብቃት ተዋህዶ በጥቅም ላይ በማዋል የአገሪቱን ኢኮኖሚ ይገነባል።

2. መሬት የህዝብ ነው የመንግስት አይደለም። መንግስት አርሶአደሩን የማይረባ ዋጋ እየሰጠ በማፈናቀል ራሱ መሬቱን በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ የሚነግድበት ስርአት መወገድ አለበት። አርሶ አደሩ መሬቱን የመሸጥና የመለወጥ መብት ይኖረዋል።

3. መሬት በቀዬው ለሚገኘው አርሶ አደር ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በየጊዜው እንዲከፋፈል ያደረጋል። እንደመሬቱ ስፋትና ለምነት በየአካባቢው(በየወረዳው) የሚመቸውን የየራሱ የመሬት አስተዳደር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

4. ያልለማ ሰፋፊ መሬት በሚመለከት አርሶ አደሩን እና አርብቶ አደሩን በማይጎዳ መንገድ መንግስት ለግል ባለሃብቶች አከራይቶ እንዲያለሙ ያደርጋል። በአካባቢው ላለው ህዝብ የስራ እድል እና ግልጋሎት (እንደ ትምህርትና ህክምና ወዘተ.) የሚሰጥ መሆን አለበት።

5. ከላይ በ ቁ. 2, 3 እና 4 የተጠቀሱት የመሬት ፖሊሲዎች ለህዝባችን አቅርበን እንዲወያይበትና እንዲወስንበት እናደርጋለን።

6. የሰራተኛውና የአርሶአደር መብትና ጥቅም እንዲጠበቅና ኑሮው እንዲሻሻል ዝርዝር ደንቦች በማውጣት ተግባር ላይ ያውላል።

7. በዋጋ ግሽበት ምክንያት የሰራተኛው ኑሮ እያንቆለቆለ ስለሚሄድ የደሞዙ እድገት በግሽበቱ አንጻር ተመጣጣኝ እንዲሆን ያደርጋል።

8. የግል ኢንቨስተሮች በንብረታቸው ላይ ለሚኖራቸው መብት ዋስትና ይሰጣቸዋል። ሆኖም ንብረቱ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት በሚኖረው አስተዋፅኦ ወደ መንግሥት ንብረትነት ቢዛወር ለባለንብረቱ ሙሉ ካሣ ይከፈላል ።

9. የኢትዮጵያ መልክአ ምድርና የህዝቡ ኑሮ ተያይዞ ሲታይ በሁሉም ቦታ አንድ ወጥ የሆነ የመሬት ይዞታ ፖሊሲ ለመቅረጽ ኣያስችልም። መሬት 85% የኢትዮጵያ ህዝብ የሚተዳደርበት የኣገርችን የኢኮኖሚ ምሰሶ በመሆኑ ትልቅ ትኩረትና እቅድ ያስፈልገዋል። በዚሁ ላይ ለኣገሪቱ ይጠቅማሉ የተባሉ የተለያዩ ኣመለካከቶች ስላሉ ትዴት በበኩሉ ኣስተማምኝና ዘላቂ እንዲሁም ህዝቡንም ያሳተፈ መፍትሄ እንዲሆን ዲሞክራሲያዊ መንግስት ከተመሰረተ በኋላ በጥናት የተድገፈ ውሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል።

10. አብዛኛው የህዝባችን ክፍል አርሶ አደር እንደመሆኑ ለእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚው ዕድገት አስፈላጊ ትኩረት ይሰጣል። በምግብ ራስን የመቻልና ድህነትን የመቀነስ ፖሊሲ ትኩረት ያገኛል።

11. በእርሻ ወሳኝ ለውጥ ለማምጣት የውሃና የመስኖ አጠቃቀም ዘዴን ማዳበርና ማስፋፋት ያስፈልጋል። በትግራይ እንዲሁም በሌላው የኢትዮጵያ አካባቢ ዝናብ በወቅቱ አለመምጣቱ ካልሆነ እህል ወይም ግጦሽ ለማብቀል በቂ ዝናብ እንደሚዘንብ ይታወቃል። ከዝናብ የሚፈሰውን ዉሃ በሚያስፈልገው መጠን ወደ ማሳ ወይም የግጦሽ ቦታ ማስገባት ይቻላል። ለዚሁ ምሳሌነት በህወሓት የትጥቅ ትግል ጊዜ ምንም ዝናብ በማይደርስበት ሽዋጣ በሚባለው ቁሸት ከአከባቢው ተራሮች የሚፈሰውን የክረምት ወንዝ በመጠቀም እንዲለማ ተደርጓል። ከዚሁ ተመክሮ በመውሰድ በክረምት ከደጋማ ቦታ የሚፈሱትን ወንዞች በመጠቀም ሰፊ የቆላ ማሳዎችንና የግጦሽ ቦታዎችን ማልማት ይቻላል። ትዴት ይህንን ተግባራዊ የሚያደርግ እቅድ ያወጣል።

12. ኣርብቶ ኣደሩ ህዝብ የከብት እርባታውን ስራ ዘመናዊ ኣያያዝ በማድረግ የተሻለ እድገት እንዲያሳይ መንግስት ከህዝቡ ጋር በመመካከር ሰፋፊ እቅዶች ነድፎ ተግባር ላይ ያውላል።

13. የአርሶ አድሩ እና የአርብቶ አደሩ ምርት እንዲሻሻል መንግስት ጥናትና ምርምር በማድረግ የምርጥ ዘርና የቴክኖሎጂ ግኝቶች እንዲኖሩ ያደርጋል፣ ያበራታል።

14. የህዝብ ብዛትና የመሬት ጥበት በሚታይበት ኣካባቢ ልዩ የስራ መስኮች በመክፈት ወይም በጥናት የተደገፈና በህዝቡ የታመናበት ሰፈራ በማዘጋጀት ችግሩ እንዲቃለል ይደረጋል።

15. የኢንዳስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲያድግ መንግስት በቅድሚያ ከሃገር ውስጥ ቀጥሎም ከውጭ ሃገር ባለ ሃብቶች ጋር በመዋዋል ወይም ዋስትና ያለው ፈቃድ በመስጠት የኣጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶቹን ተግባር ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

16. የሓይል ምንጮች፥ ደኖች፥ የማእድንና የውሃ ሃብት የመሳሰሉ የተፈጥሮ ሃብቶች መንግስት እየተቆጣጠረ ላገሪቱ ኣጠቃላይ እድገት ያውላል።

17. መብራት ሓይል፥ ፖስታ፥ ቴሌፎን፥ ኣውራ ጎዳና የመሳሰሉ ኣበይት ግልጋሎት ሰጪ ተቅዋማት ለሃገሪቱ ዘላቂ እድገት በሚያመች መንገድ መንግስት ያስተዳድራቸዋል ለግል ባለ ሃብቶችም ክፍት ይሆናሉ።

18. ቱሪዝም ትለቅ የስራ መስክና የውጭ ምንዛሬ ማስገቢያ ሊሆን ይችላል፣ ስለሆነም ትኩረት እንዲሰጠው ይደረጋል።

19. የትግራይ መሬት ለረዥም ጊዜ በግብርና የቆየ በመሆኑ የመሬቱ ለምነት በጣም ተዳክሟል። እንዲሁም ደኑ በተለያዩ ምክንያቶች ከሚገባ በላይ ተመንጥሯል። አሁን በዓለም ደርጃ ካለው የአካባቢ አየር ብክለት ጋር ተዛምዶ ትገራይ በቀላሉ በድርቅና በርሃብ የሚጎዳ አካባቢ ሆኗል። ለዚሁም ትኩረት ተሰጥቶት ያካባቢ ተፅእኖ(environmental impact) ለመቀነስ ብሎም ደንን ለማስፋትና የአየር ብክለትን ለመቀነስ ይሰራል።

20. በእርሻም ሆነ በኢንዱስትሪ የግል ኢንቨስትሮች ሃብታቸውን ኣሰማርተው የሚያለሙበት፣ ራሳቸውም ትርፍ የሚያገኙበት ኣስተማማኝና በሕግ የተደገፈ ደንብ ስራ ላይ ይውላል።

21. በሃገር ውስጥ ካሉትና ከውጭ ሃገሮች ከሚመጡት ኢንቨስተሮች ጋር የሚደረገው የንግድ እንቅስቃሴ የግል ጥቅምንና የአገር እድገትን በሚያጎለብት መንገድ ነጻ ሆኖ እንዲስፋፋ መንግስት ያበረታታል።

22. ከጎረቤት አገሮች ጋር በጋራ ማደግንና መጠቀምን መርሆ ላይ መሰረት ያደረግ የንግድና የኢኮኖም ትስስር እንዲኖር ያደርጋል።

23. በመላው የሃገሪቱ ክፍል የተመጣጠነ እድገት እንዲኖር በልማት ወደ ሁዋላ የቀሩትን ኣከባቢዎች ኣስፈላጊ ድጋፍ በማድረግ እድገታቸው እንዲፋጠን የሚያደረጉ እርምጃዎችን ይደግፋል/ያበረታታል።

24. ብዙ ገንዘብ የማናወጣበትና የህዝባችን ቁርጠኝነት የሚጠይቀውን ሙስናን እና ጉቦን መቆጣጠር ነው። ባለፉት 27 ዓመታት ከኢትዮጵያ ያለአግባብ ወደ ውጭ የወጣው/የተሰረቀው ገንዘብ $36 ቢልዮን (የአሜሪካ ዶላር) መሆኑ ይገለጻል። ከዚሁ ሌላ በአገር ውስጥ በጉቦ የሚመዘበረው ገንዘብ እና በጊዜ የሚጓተቱት ጉዳዮች መመዘኛ የለውም። ይህን በሙስና የሚጠፋው የገንዘብ መጠን እና የጊዜ መባከን ስንመለከት ለአገሪቱ እድገት ምን ያህል ትልቅ ኣስተዋጽኦ ሊኖረው እንድሚችል መገመት አያዳግትም። ይህ ሁኔታ በአጭር ጊዜ ማቆም አለብን። መንግስት በህግ መቆጣጠር እንዳለበት የማያከራክር ቢሆንም በቁጥጥር ላይ ህዝቡ ወሳኝ ሚና እንዳለው በመገንዘብና ህዝቡን ማስተማርና መቀስቀስ ያስፈልጋል። ህዝቡ፣ጋዜጠኛው፣ ሲቪክ ማህበሮች፣ ባለሙያዎች፣ ወዘተ. ሙስናን ለማጋለጥና ለማጥፋት ሚናቸውን እንዲጫወቱ መጀመሪያ ዲሞክራቲክ ስርዓት መፍጠር ወሳኝ መሆኑን ትዴት ይገነዘባል። ህዝቡ ያለፍራቻ ማጋለጥ ሲችልና ፍርድ ቤቶችም ያልምንም ጫና ህግ ለማስፈጸም ሲችሉ ብቻ ግባችንን ልንመታ እንችላለን። ትዴት ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በሙሉ ቁርጠኝነት ይነሳል አስፈላጊውን መዋቅር፣ ህጎችና ደንቦች ኣንዲዘጋጁም ያደርጋል።

## <u>ክፍል III</u>

### <u>ማህበራዊ ጉዳይ</u>

1. የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪካዊ ሂደቱ ያዳበራቸው ገንቢና ኣኩሪ ልምዶች፤ ቅርሶችና የስነ_ጥበብ ውጤቶች ተጠብቀው እንዲኖሩና እንዲዳብሩም ኣስፈላጊ እንክብካቤ ያደረጋል።
5. በፆታ፥ በሃይማኖት፥ በዘርና በብሔር . . . ወዘተ የተመሠረተ ልዩነትን በማስወገድ ለእኩል አገልግሎት እኩል ክፍያ ዋስትና ይሰጣል ።
6. የሃገሪቱ ኣጠቃላይ እድገት የሚያቀላጥፍ፤ በጎ ባህልን የሚያዳብር፤ የህዝቡ መሰረታዊ ፍላጎትን ያካተተ ስርኣተ ትምህርት ተቀርጾ ተግባር ላይ ይውላል።
4. ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የመማር ግዴታ ያለበት ነፃ የትምህርት ዕድል

ለማቅረብ አስፈላጊ ጥረት ይደረጋል ። የህዝቡ ኢኮኖምያዊ ደረጃ እስኪሻሻል ድረስ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርትም በነጻ የሚሰጥበት ሁኔታ ማመቻቸት።

7. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዳብሮ ህዝቡ የእድገት ተጠቃሚ የሚያደርግ የጥናትና ምርምር ማእከላት እንዲስፋፉ ይደረጋል።
8. የጤና ጥበቃ አገልግሎት በሃገሪቱ ገጠሮችና ከተሞች እንዲስፋፉ የሚስችል አስፈላጊ እርምጃዎች ሁሉ ይወሰዳል።
9. ህክምና አስቀድሞ ከበሽታ መከላከልን የሚያጠቃልል ብቃት ያለው የጤና አገልግሎትና ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል።
10. ጥንታዊ መድሃኒትና የህክምና ጥበባት ከዘመናዊ ህክምና ተቀናጅቶ አገልግሎት ላይ የሚውልበት ዘዴ ተጠንቶ ተግባር ላይ ይውላል።
11. ሁሉም አከባቢዎች ባህላቸውን ለማዳበርና ለማስተዋወቅ ይበረታታሉ። የመንግሥት ድጋፍ ያለምንም አድልዎ ለማግኘት ሁሉም መብት አላቸው ።

## ክፍል IV

## የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

1. የሃገሪቱ ሉኣላዊነትንና የህዝቡ መሰረታዊ መብቶችን በማስከበር ላይ የተመሰረተ የውጭ ጉዳይ መርህ ይከተላል።
2. በሌላ ሃገር ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ያለመግባት ፖሊሲ ይኖራል ።
3. የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባልነትን መቀጠልና ዓለም አቀፍ ሕጎችን በቅንነት ማክበር።
4. ከልዩ ልዩ አገሮች ጋር በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ያደረጋል ።
5. ከሌሎች አገሮች ጋር የተደረጉ ያልተመጣጠነ ወታደራዊ ውሎች ማስወገድ ። የውጭ ወታደራዊ ተቋማትን መዝጋትና ባለፈው መንግሥት ይህንን በሚመለከት የተፈረሙ ውሎች ካሉ እንዲሰረዝ ያደርጋል ።

## ክፍል V

## ስለ ሃገራዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር

በኢትዮጵያ ለሰላምና እድገት ቅድመ ሁኔታ የሆነው ዘላቂ ዴሞክራስሲያዊ ሥርዓትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሰፊ መሰረት ያለው የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ትብብር አስፈላጊ ነው ። በአሁኑ ወቅት በአገራችን የግንባር አስፈላጊነት ከምን ጊዜም በላይ ወሳኝ እየሆነ በመምጣቱ የተለያዩ ኢትዮጵያዊያን ኃይሎች በመለስተኛ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም ሥር እንዲተባበሩና የሃገር ግንባታው በጋራ እንዲጀምሩት ት.ዴ.ት ጥሪ አቅርበዋል ። በግንባር ምስረታ ብቻ ሳይወሰንም፤ የድርጅቶች ጋጋታ ተቀንሶ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጉዋትን የተወሰኑ በሃገራዊ መርሆች ላይ የተወሃሃዱ ሃገር አቀፍ ፓርቲዎች እንዲፈጠሩ ጥሪ አቅርቦ ለተግባራዊነቱ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ት.ዴ.ት ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር ሁሉ ውይይትንና መቀራረብን ብቻ ሳይሆን ውህደትንም ይሻል ።

ኅዳር 27, 2012